12ኛ ዓመት ቁጥር 6
12th Year No. 6

ባህር ዳር ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ/ም
Bahir Dar 7th May, 2010

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 10.80
Unit price

| ማውጫ | Contents |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 170 /2002 ዓ.ም<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስለተፈቀደ የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና የወጣ አዋጅ | Proclamation No 170 /2010<br>A Proclamation Issued for Domestic Loan and Guaranty authorization of the Amhara National Regional State |

**አዋጅ ቁጥር 170 /2002 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስለተፈቀደ የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና የወጣ አዋጅ**

የክልሉን የግብርና ልማት ለማፋጠን የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ራሳቸውን ችለው መበደር ለማይችሉ ደሃ አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎት ማመቻቸት እና የክልሉን አርሶ አደር የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

**Proclamation No 170 /2010**

**A Proclamation Issued for Domestic Loan and Guaranty authorization of the Amhara National Regional State**

WHEREAS, it has become necessary to promote the product and productivity of farmers with a view to enhancing the agricultural development of the Region;

WHEREAS, it is found appropriate to facilitate credit service for poor farmers who are not capable of borrowing by themselves and thereby ensure food security of the Region;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ /49/ ንዑስ አንቀጽ /3/ /1/ እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /33/ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional State, in accordance with the power vested in it under Article 49 Sub Article 3/1 of the revised constitution of the Region and Article 33 of the Regional Finance Administration Proclamation No. 18/1997 /as amended/ hereby issues this proclamation.

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና መፍቀጃ አዋጅ ቁጥር 170 /2002 ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as “The Amhara National Regional State Domestic Loan and Guaranty Authorization Proclamation No. 170/2010.”

## 2. <u>ስለ መበደር</u>

የክልሉን የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ለ2002/2003 የመኸር፣ የመስኖና የበልግ የምርት ዘመን በኤክስቴንሽን ለተለያዩ ፓኬጆች ማስፈፀሚያ የሚውል ለግብዓትና ለግብርና ምርት ግብይት ብድር በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስም ከብር 1,474, 808,989 ( ከብር አንድ ቢሊዮን አራት መቶ ሰባ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ) ያልበለጠ ገንዘብ ከአገር ውስጥ ባንኮች ለመበደር ለጊዜው ከአርሶአደሩ የተሻለ ቁርኝትና ብድር የማስተዳደር ብቃት ካላቸው ተቋማት ማለትም መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች እንዲሁም ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር የትብብር ስምምነት በማድረግ ዋስትና ለመስጠት ተፈቅዷል፡፡

## 2. <u>Loan</u>

With a view to promoting the agricultural product and productivity of the Region a loan to be used for the purchase of various agricultural product enhancement inputs in the 2010/2011 Meher, *Messno* and Belg harvest seasons is hereby authorized to give guaranty for creditors such as cooperative societies and unions as well as the Amhara Credit and Saving Institution to borrow an amount of money not exceeding Birr 1,474,808,989 (One Billion Four Hundred Seventy Four Million Eight Hundred Eight Thousands Nine Hundred Eighty Nine Birr) from Domestic Banks on behalf of the Amhara National Regional State by having concluded cooperation agreement with these institution due to the fact that they have currently closest ties with the farmers as well as efficiency to manage the loan on their behalf.

## 3. <u>ብድር አመላለስና የጊዜ ገደብ</u>

ሀ. በዚህ የብድር አዋጅ መሰረት የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የክልሉ ወረዳዎች የወሰዱትን የብድር መጠን ከመመለሻ ጊዜ ገደቡ በፊት የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

ለ. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ እና አግባብ ያለው የወረዳ አስተዳደር ብድሩን የማስመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

ሐ. ብድሩን የሚያስተዳድሩ አካላት የብድር ስርጭትና አመላለሱን በተመለከተ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተፈላጊውን መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

መ. ለመኸር ምርት የሚሰጠው ብድር እስከ ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም፣ ለግብርና ምርት ግብይት፣ ለበልግና ለመስኖ የሚሰጠው ብድር ደግሞ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሚመለስ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስልጣን</u>

የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተወሰደውን ብድርና የተፈቀደውን ዋስትና እየተከታተለ እንዲያስፈፅም በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 3. <u>Return of Loan and Time Limit</u>

a. Woredas of the region that are beneficiaries of the loan, pursuant to this proclamation, shall be duty bound to return the amount they have borrowed before the time limit for the credit settlement.

b. The Agricultural and Rural Development Bureau and the Woreda Administration shall be duty bound to return the loan.

c. Bodies that administer the loan are required to provide the necessary information concerning loan distribution and return to the Finance and Economic Development Bureau.

d. Loans to be offered for *Meher* harvesting season shall be returned until July 30,2003 Ethiopian calendar; and the loan to be provided for the purchase of agriculture products marketing and for Belg and *Messno* harvesting seasons shall be paid back until December 30,2004 Ethiopian calendar.

## 4. <u>The Power of Finance and Economic Development Bureau</u>

The Regional Finance and Economic Development Bureau is vested with power by this proclamation to follow up the implementation of the loan and the authorized guaranty.

## 5. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 6. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ.ም**
**አያሌው ጎበዜ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት**

## 5. Power to Issue directive

The Council of the Regional Government may issue directive necessary for the complete implementation of this proclamation.

## 6. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**
**This 7th day of May 2010.**
**Ayalew Gobezie**
**President of the Amhara National Regional State**